

# ውሃ ይቆጥቡ፣ ገንዘብ ይቆጥቡ

ትናንሽ የሆኑ ለውጦችን ማድረግ በአካባቢ እና በወርሃዊ ክፍያዎት ላይ ለውጥ ያመጣል።

- ሻወር የሚወስዱበትን ጊዜ ወደ 5 ደቂቃ ማሳጠር በቀን እስከ 10 ጋሎን የሚሆን ውሃ ለመቆጠብ ያስችላል።
- የውሃ እና የፍሳሽ ክፍያዎችዎን ከ 35–55% በሚሆን መጠን ለመቀነስ ከፍተኛ ብቃት ያላቸው መጸዳጃ ቤት፣ የማዕድ ቤት እቃ ማጠቢያ እና የልብስ ማጠቢያ ማሽኖችን ይጠቀሙ።
- የሚያንጠባጥብ (የሚያፈስ) መጸዳጃ ቤት በቀን እስከ 200 ጋሎን የሚደርስ ውሃ ሊያባክን ይችላል። በውሃ ማጠራቀሚያው ውስጥ የምግብ ማቅለሚያ በመጨመር ፍሳሽ ካለ ይመርምሩ—ቀለሙ ወደ ፖፖው ውስጥ መጥቶ ከታየ፣ ይህ ፍሳሽ እንዳለ ያረጋግጣል።

AlexRenew

عرض بالعربية



# የክረምት ሩብ ዓመት አማካይ ምንድን ነው?

የክረምት ሩብ ዓመት አማካይ ማለት አንድ ደንበኛ ከዲሴምበር እስከ ፌቡራሪ ወራት (የክረምት ሩብ ዓመት) ያለው የውሃ አጠቃቀም ታሪኩ ታይቶ በዚህ ላይ ተመስርቶ የሚሰራ የክፍያ ጣራ ነው። ይህ የክፍያ ጣራ ደንበኞች ለቤት ውስጥ የውሃ ፍጆታቸው ብቻ መክፈላቸውን ለማረጋገጥ ይጠቅማል — ይህም ማለት በቤት ውስጥ ጥቅም ላይ ውሎ ወደ AlexRenew የቆሻሻ ውሃ ማከሚያ ጣቢያ የሚሄደው ውሃ ማለት ነው።

ብቁ የሆኑ ደንበኞች ከማርች እስከ ኖቬምበር ላለው ጊዜ ለትክክለኛ የውሃ ፍጆታቸው ወይም የክረምት ሩብ ዓመትን በመጠቀም፣ ከሁለቱ ዝቅ ባለው፣ እንዲከፍሉ ይደረጋሉ።

ከሚከተለው ላይ የበለጠ ይወቁ፥ **alexrenew.com/winteraverage**

ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ይከተሉን